ዘርፍ 1

በወረዳ መስተዳደር መሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ዘርፍ 2

የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦት፣

ዘርፍ 3

ዜጎች በክልሎችና በወረዳዎች በጀት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማስፋት፣

ዘርፍ 4

የህብረተሰብ ተጠያቂነት ፕሮግራም ናቸው፡፡

የከለላ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ፕሮጀክት ዘርፍ የሆነው የህብረተሰብ ተጠያቂነት፤ አላማው የህብረተሰብ ተጠያቂነት ማዳበሪያ መንገዶች በዜጎችና በማህበረስብ ድርጅቶች ተጠናክረው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግና የበጀት ቀመር ሂደትን ግልጽ በማድረግ ባልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በብቃት እንዲሳተፉ ማስቻል ነው፡፡ በግንቦት 1999 በኢትዮጵያ መንግስትና በአለም አቀፍ የልማት አጋሮች የተመሰረተው የኢትዮጵያ ለህዝብ ተጠያቂነት ፕሮግራም ድጋፍ የማሰባሰብ ስራ ኢትዮጵያ የምዕተ - አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የምታደርገውን ሂደት ለመደገፍ የታቀደ አዲስ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዜጎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች ማህበራዊ ተጠያቂነትን በመጠቀም መሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ብቃትና ጥራት ያለውና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲያደርጉ ማበረታታት የሚያስችል ዘዴ ነው ማለት ያስችላል፡፡

ስለሆነም የማህበራዊ ተጠያቂነት ዓላማ ዜጎች/የዜጎች ማህበራት በየአካባቢያቸው ስለሚያገኙት መሠረታዊ አገልግሎት ድምፃቸውን የሚያሰሙበትንና የሚጠይቁበትን ግንዛቤ መፍጠርና አግባብ ያለውን ዘዴ በሙከራ መለየት ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር /አልማ/ በዋና አስተባባሪነት ከአማራ ሴቶች ማህበር፣ ከግሪን ቤልት የተቀናጀ የማ/ል ድርጅት እና ከፓክት ኢትዮጲያ ጋ ር በመተባበር በክልሉ ሁለት የከተማ አስተዳደሮችና ሁለት የገጠር ወረዳዎች የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክትን ለሙከራ ተግብሯል፡፡ ሙከራው የተተገበረባቸውም በደ/ማርቆስ እና በዳንግላ ከተማ አስተዳደሮች ስድስት ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና የጤና ተቋማት ናቸው፡፡ በተመሳሳይ፣ በፋርጣ እና በመተማ ወረዳዎቸ በሰድስት ቀበሌዎች የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና ጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ የፕሮጀክቱ አካል ነበሩ፡፡

የህብረተሰብ አኃዝ ካርድ

የህብረተሰብ አኃዝ ካርድ ህብረተሰብ ተኮር የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ሲሆን፣ በተለይም በአገልግሎት አሰጣጥና በተጠሪነት ላይ ያነጣጠረ፣ በአገልግሎት ሰጭና በህብረተሰብ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያጠቃልል

ሆኖ፣ ፈጣን አስተያየት የሚጠይቅ ፣ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራትና ብቃት የሚመዝን ነው፡፡ ጥቅሙ ለአካባቢው ሆኖ፣ ህብረተሰቡ መስፈርት ስለሆነ፣ በተተኮረባቸው ክፍሎች በኩል የተሰበሰቡ ጥራት ያላቸው መረጃዎች ከሁሉም ባለድርሻ አካሎች (የሚያገባቸው) ተሳትፎ ጋር የድህነት ማስወገድ ስልቶችን ውጤታማነት ለመገምገም፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሻሻልና የተሻለ ቁጥጥር አበጅቶ የተዘረጋውን ዕቅድ ለመፈጸም፣ የልዩ ልዩ ባለድርሻዎችን የጠለቀ አስተሳሰብ ለመገምገም፣ ሁኔታውን ለማሻሻል ምን መደረግ እንዳለበት በአንድነት ሆኖ ለመወሰን፣ ህብረተሰቡ መለኪያ ስለሆነ ጥራት በተተኮረባቸው ክፍሎች/ቡድኖች/ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተግባር ላይ ለማዋል የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡

አሳታፊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት

ሕብረተሰቡ በመንግስት በጀት አሰራር ላይ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያስችል የማህበራዊ ተጠያቂነት ማስፈጸሚያ ዘዴ ነው፡፡ በጤና እና ትምህርት አገልግሎቶች ላይ በማተኮር የአካባቢው ተፈጥሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ከመለየትና ከመተንተን አንስቶ፣ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዳ ዓላማ በመንደፍ፣ በዚሁም መሰረት ዝርዝር ተግባራትን በመለየት፣ ዕቅድ ማዘጋጀትን እና ለዕቅድ



ተማሪዎች በትምህርት በጀት ጉዳይ ላይ ሲወያዩ

ማስፈፀሚያ በጀት ማዘጋጀትና የየአካላቱን ድርሻ፣ የስራ ሃላፊነትና የበጀት ምንጭ እስከመግለፅ ድረስ የሚሳተፍበት ሂደት ነው።

በዚህም መሠረት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት የማህበራዊ ተጠያቂነት ማሳለጫ ዘዴዎች በመጠቀም በተመረጡት የከተማ አስተዳደሮች/ወረዳዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች /አዋቂ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የማህበረሰቡ ተወካዮች/ ከ10-20 ሰዎች በቡድን በመሆን በየአገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ በአካል ይገኛሉ። በየአካባቢያቸው የሚያገኙትን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተገቢነት ይፈትሻሉ፣ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ከመንግስት የትምህርትና ጤና ፖሊሲ አንፃር ይቃኛሉ። አገልግሎቶቹን ለማሻሻል የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የመንግስትና የህብረተሰቡን አዲስ አጋርነት ከማጉላት ባሻገር፣ መንግስት ለብቻው የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት እንደማይችልና ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

በዚህ አጭር ቅኝት በጥቂቱም ቢሆን የሙከራ ፕሮጀክቱን ትገበራ በዓይነ-ህሊና እንድንቃኝ ያስቸለን ዘንድ በፕሮጀክቱ ተሳትፎ ከነበራቸው አንድ አባት ጋር ቆይታ አድርገናል።

የመኝታን ምቾት የሚያውቀው ያነጠፈው ወይስ የተኛበት?

አቶ ሙሉዓባይ ታምሩ በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ 03 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በመምህርነት ሙያ ለረጅም ጊዜ እንዳገለገሉና አሁንም በሥራ ላይ እንደሆኑ ነግረውኛል።

ስለ ከለላ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕርጀክት ምንነት፣ ዓላማና ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁውጤቶች...ወዘተ ለማስተዋወቅ የፕሮጀክቱ የክልል እና የከተማ አስተዳደሩ ባለሙያዎች እና የፕሮጀክቱ ፈፃሚ ድርጅቶች በደብረማርቆስ ከተማ ሲኒማ አዳራሽ ተገኝተናል። በወቅቱም ከቀበሌ 03 ለመጡ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ተገቢውን ግንዛቤ አስጨብጠን፣ ጠቃሚ ውይይቶችን አድርገናል። ፕሮጀክቱ ሲተገበር የሚመሰረቱት የውይይት ቡድኖችን በማስተባበር አመቻቺ የሚሆኑ ሁለት-ሁለት ሰዎችን ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ አስመርጠን እና ሌሎችና ቀጣይ የፕሮጀክቱን ሥራዎች ገልጸን አዳራሹን ለቀን በመውጣት ላይ እንዳለን ከኒላዬ ሙሉ ጥንካሬና አጥንተ ስፊ የሆነ እጅ ትከሻዬ ላይ አርፎ አንገቴን እንዳዞር አስገደደኝ፣ ዞርኩም።

"ሙሉ ዓባይ ታምሩ እባላለሁ" አሉኝ። "ምን ልርዳዎት?" አልኳቸው። "ና እስኪ ወዲህ?!" ብለው በአባታዊ መንፈስ ወደ አንድ ነፃ ቦታ ወሰዱኝ። እርምጃቸው ዝግ ያለ፣ጥሞናቸው ጥያቄን የሚጭር ሆኖ አገኘሁትና "ምን ሊነግሩኝ? አለያም ሊጠይቁኝ አስበው ይሆን?" ስል ከራሴ ጋር ተነጋገርኩ። ቆም እንድንል እጄን ያዝ አደረጉኝና በትኩረት ተመለከቱኝ። "ልጄ!" ብለው ጀምረው ያጫወቱኝን እንደወረደ ይኸውላችሁ።

ስታነቡትም በአስተውሎት ይሁን፡፡

“ልጄ! እንደምታየኝ ዕድሜዬ ብዙ ነው፣ በዕድሜዬም ሦስት መንግሥታት ተፈራርቀውብኛል፡፡ እስካሁን በኖርኩት ዕድሜዬ ውስጥ ግን እንዲህ እስከ ቀበሌ ድረስ ወርደው የሚያስተዳድሩትን ህዝብ የሚያወያይ አካል እንዲኖር ሲፈቅዱ አላስተዋልኩም፡፡ ቅድም ለምን እንደመጣችሁ፣ ዓላማችሁ ምን እንደሆነ ተረድቼ ሳበቃ ግን አንድ የአባቶችን ተረት ልነግርህ ወደድኩኝ” አሉኝ፡፡

“ልጄ!” አሉኝ አሁንም በድጋሚ፡፡ “ተረቱን ከመንገሬ በፊት ግን አሁን እናንተ ይዛችሁት ከመጣችሁት የፕሮጀክት ሃሳብ አንፃር መረዳት እንዲቻልህ ልብ ብለህ አድምጠኝ !እንዳትረሳም!” ካሉኝ በኂላ ለአፍታ አሰብ አደረጉና፣ “እኔ እንደሚገባኝ መንግሥት ለህብረተሰቡ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ብዙ ናቸው፡፡ብዙ እንደመሆናቸው መጠን ደግሞ የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያረኩም ላያረኩም ይችላሉ፤ አይደለም እንዴ ልጄ?” ሲሉ ጠየቁኝና ንግግራቸውን ገታ አደረጉ፡፡ “እርግጥ ነው!” በማለት ሃሳባቸውን መጋራቴን አንገቴን ወደላይና ወደታች በመነቅነቅ አረጋገጥኩላቸው፡፡

ይሄኔ ነው ታዲያ “አገልግሎት እናገኛለን፡፡ነገር



ስለበጀት ሕዝብን ለማስተማር በአልማ የተሰማሩ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ የህግ ተማሪዎች

ግን በቂ አለያም ተገቢ መሆን አለመሆኑን ከእኛ ከተጠቃሚዎች የበለጠ የሚያውቀው የለም! ለማለት ተረቱን የተጠቀሙበት:: "ካነጠፈ የተኛ ያውቀዋል!" ሲሉ ተረቱና፣ "ደህና ሁን ልጄ ሰላም ያገናኘን..." ብለው ተለዩኝ::

ተረቱን እያብሰለሰልኩ በቆምኩበት ቀረሁ:: አግራሞቴ ሳያልቅ አቶ ሙሉዓባይ ያጫወቱኝን ለሥራ ባልደረቦቼ እያወራሁ ጉዞ ወደ



ሌሎች ፕሮጀክቱ የሚተገበርባቸው ዳንግላ፣ፋርጣ እና መተማ ሆነ::

በነገራችን ላይ በማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠያቂነት የሙከራ ፕሮጀክት አልማና አጋሮቹ :-

1. ዜጎች የመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥን የበለጠ ግብ መቺ፣ውጤታማ፣መልስ ሰጪ እና ተጠያቂነት ያለበት በማድረግ የማሕበራዊ ተጠያቂነት አሰራርን እንደ አንድ መሳሪያ እንዲጠቀሙበት በማሳወቅ፣

2. ዜጎች ስለበጀትና ስለበጀት ሂደቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማዳበር እና የተሳታፊነት አቅማቸውን በማጎልበት፣ የማሕበራዊ ተጠያቂነትን የሙከራ አሰራር ዕቅድ በማውጣት፣ የተገኙ ልምዶችንና ትምህርቶችን ለሌሎች በማስተላለፍ፣ የተገኙ ውጤታማ ማሕበራዊ ተጠያቂነት አሰራረሮች የሚስፋፉባቸውን ሁኔታ በመፍጠር፣

3. ዜጎች ከመንግስት በሚሰጡ አገልግሎቶች ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች በተመለከተ ግንዛቤ በማዳበርና ቀጥተኛ ድጋፍ በመስጠት፣ የሚሰሩ የሙከራ ሥራዎች በተገልጋዮች ላይ ያተኮሩና በመንግስት የአገልግሎት ሰጪና በተገልጋዮች መካከል እንደ ድልድይ በማገልገል ረገድ ሚናቸውን በአግባቡ እንደተወጡ ልብ ይሏል::

እንዲህም ሆነ! በፕሮጀክቱ ከየቀበሌ አስተዳደሮቹ በየቀበሌው ማህበረሰብ የተመረጡ አመቻቾች፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሃላፊዎችና ሌሎችም ሥልጠና ወስደዋል:: በየሚያስተባብሯቸው የየውይይት ቡድኖች ውሥጥም ከ10-20 ሰዎችን አደራጅተው፣ በየአካባቢያቸው በሚያገኟቸው መሠረታዊ አገልግሎቶች ተገቢነት ዙሪያ ድምፃቸውን ማሰማት የመቻል አቅም መገንባታቸውን በማረጋገጥ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ከየአካባቢያቸው የውሳኔ ሰጪ የመንግስት አካላት ጋር ገፅ ለገፅ ውይይት አድርገዋል:: የጋራ መግባባት ላይም ደርሰዋል:: ፕሮጀክቱ ቀጣይና ዘላቂ የሚሆንበትን ሁኔታ በጋራ መክረውና ዘክረው ከየቀበሌውና ወረዳ/ከተማ መስተዳድሮች እና ከሕብረተሰቡ የተውጣጣ ግብረ-ሀይል አቋቁመዋል:: በተጨማሪም ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀውን ውጤት አሟልተው ተመክሯቸውን ለሌሎች ቀበሌዎችና አቅራቢያ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች ለማካፈል ቃል ገብተዋል::

በዚህ ሁኔታ የፕሮጀክቱ የሙከራ ጊዜ በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የተጠናቀቀ ዕለት እንዲህ በሆነ ስል ተመኘሁ! 'ፕሮጀክቱ የሙከራ ነውና፤ የተመደበለት የጊዜ ገደብ ደርሶ ከአቶ ሙሉ ዓባይ ጋር ፕሮጀክቱ ሲጀመር እንደተገናኘን ሁሉ፤ በማጠቃለያው ተገናኝተን አንድ ተረት ጣል ቢያደርጉልኝ::"

ለዚህ ምክንያት አለኝ:: ሰውየው በቀበሌያቸው በሚገኘው የማህበረስብ ውይይት ቡድን አመቻች ናቸው:: እንዳስተዋልኳቸው ነገሮቻቸውን በተረት ነው የሚያጠቃልሉት:: ለዚህ ነው ተረታቸውን መሻቴ:: የተረታቸውን መሻቴን ያወቁ ይመስል፤ አቶ ሙሉዓባይ እኔና የሥራ ባልደረቦቼ ወደአረፍንበት ሆቴል ከሙሉ ፈገግታ ጋር ሲመጡ አስተዋልኳቸው:: ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላም... በሥሜ ጠሩኝና "አጭር ለማይባል ጊዜ አብረን ቆየን፤ ቤተሰብም ሆነናል:: ፕሮጀክቱን ስንጀምር እንደነገርኩህ ያለ ዛሬም በምትወደው ሥነ-ቃል ፤ ነገር ግን ከፕሮጀክቱ ያገኘነውን ትምህርት ጭምር የሚገልጽ ተረት እነግርሃለሁ"

አሉኝ:: እንዴት ደስ እንዳለኝ ! "አያችሁ… አባቶች 'አንድ ማገር አያቀብል ቤት አስፋ ይላል' ይሉት አባባል አላቸው…የእኛም ነገር ይኸው ነው" ሲሉ ተናገሩ::
ትዕግስት ያጣው ጓደኛዬ "ምን ማለት ነው" ሲል ጠየቃቸው::"ይህማ ግልፅ ነው.." አሉን በሙሉ በራስ የመተማመን መንፈስ:: ቀጠሉና "ለምሳሌ. እኔ እስከማውቀው ድረስ መንግስት በራሱ ገንዘብ የለውም:: ገንዝብ የሚያገኘው ከህዝቡ ከሚሰበስበው ግብር፣ ከዕርዳታና በብድር ነው:: ይህንኑ ሰብስቦም የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ያሟላል:: አይደለም እንዴ?" አሉን:: መምህር ናቸውና የተናገሩት ሁሉ ለአድማጮቻቸው በትክክል መድረሱን ሳያረጋግጡ አያልፉም:: አንገታችንን ወደላይ ወደታች በማድረግ አረጋገጥንላቸው:: በማስከተልም፣ ቊጭት ባዘለ አነጋገር "አሁን በእኔ ሞት ከመንግስት ሰራተኛ፣ አንዳንድ ድርጅቶችና ከአንዳንድ ታማኝ ነጋዴዎች በሥተቀር ግብሩን በአግባቡ የሚገብር አለ?" የሚል ጥያቄ ሰነዘሩ:: "ሌላ የፕሮጀክት ሃሳብ…" በሚል የመግባባት መንፈስ ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ተያየን::

"ሌላም አለ! ድሃው ህብረተሰብ ገንዘብ ባይኖረው ጉልበት አለው:: በአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት አለው:: መንግሥትስ ይህን በማስተባበር መጠቀም አይችልም? ህብረተሰቡስ እኔ ይህ አለኝ ብሎ መንግስት ደግሞ የጎደለውን ያሟላልኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም!? አዎ ይቻላል! በዚህ ፕሮጀክትስ ያየነው የተማርነው ይህንኑ አይደለም?!" አሉንና፣ "በሉ !…ወደ እኔ ቤት ሄደን ቤት ያፈራውን ብትቀምሱልን ደስ ይለኛል? " ሲሉም ግባዣቸውን አቀረቡልን::

ሥራ እንዳለን ነገርናቸውና ተግባባን:: በመጨረሻም፣ "ወገኖቼ ሥራ እንዳላስፈታችሁ፣ እናንተ ደክማችሁ ይኸው መንግስትና ህብረተሰቡ ፊት-ለፊት ተገናኝቶ የጋራ መግባባት ላይ ከመድረስም አልፎ ፣ በመሰረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ላይ የተስተዋሉ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት መዘጋጀቱን ማረጋገጫ ሠጥቷችኋል:: እንኳን ደስ አላችሁ! እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!" ብለውንና ትከሻ ለትከሻ ተሳስመን ተለያየን::



የገጽ ለገጽ የውይይት መድረክ (ፋርጣ ወረዳ)

በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ላይ ስልጠና ሲሰጥ (ጎርጎራ)

እኔና የሥራ ባልደረቦቼ ግን "አንድ ማገር አያቀብል ቤት አስፋ ይላል"ን ከአሳታፊ ዕቅድና የበጀት ዝግጅት ሥራ ጋር "ካነጠፈ የተኛ ያውቀዋል" ከህብረተሰብ አሃዝ ካርድ ከሚባሉት የማሕበራዊ ተጠያቂነት ማስፈኛ/ማሳለጫ ዘዴዎች ጋር እያስተያየንና እየተወያየን ሀገራችን ኢትዮጵያ ተሳትፎን ማረጋገጥና አገልግሎትን መመዘን በሚያስችል የዕምቅ የሥነ-ቃል ባለሃብት መሆኗን እያወጣን እያወረድንና እያደነቅንም ለቀጣዩ የቤት ሥራ በዝግጅት ላይ ነን፡፡

ይህንን አጭር ቅኝቴን ወ/ት ሰብለ በቀለ በሚባሉና በመተማ ወረዳ መቃ ቀበሌ ነዋሪ በሆኑትና በዚህ ፕሮጀክት የቀበሌያቸው የሴቶች የቡድን ውይይት አመቻቺ ስለፕሮጀክቱ በሰጡት አስተያየት ላጠቃልል፡፡" ይህ ፕሮጀክት…." ይላሉ አስተያየታቸውን ሲጀምሩ"..ይህ ፕሮጀክት ህብረተሰቡንና መንግስትን ያቀራርባል፡፡ በተለይም በመሠረታዊ አግልግሎቶች የበለጠ ተጠቃሚም ተጎጂም ሴቶች እንደመሆናችን መጠንም ከወንዶች እኩል በፕሮጀክቱ መሳተፋችን አቅማችንን ገንብቶልናል፡፡..ፕሮጀክቱም ቀጣይነት ቢኖረውና ሌሎችም አካባቢዎችን በስፋት የሚሸፍን ቢሆን የበለጠ ጠቃሚ ነው…"

እኔም አጭር ቅኝቴን በዚሁ አጠናቀቅኩኝ፡፡ ነገር ግን …አንባቢዎቼን አልማ በእንደዚህ ያለ ፕርጀክት ላይ በመሳተፍ የሕዝብን ተሳትፎ ለማጎልበት የበኩሉን እየተወጣ መገኘቱ ኩራት እንዲሰማኝ ማደረጉን እና ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ሆነን ይህንን የሙከራ ፕሮጀክት ውጤታማ በማድረጋችን እንደረካሁ ሳልደብቅ እየነገርኳችሁ በፕሮጀክቱ የተዘጋጀውን ዶክመንታሪ ፊልም፣ ፎረም ሲኒማ ና ሌሎች ዶክመንቶችን እንድትመለከቱ በመጋበዝ ተሰናበትኩ፡፡

ቸር ይግጠመን
አድማሱ ተፈራ
Admish96@yahoo.com

ሕዝብ አሳታፊ የልማት ርብርብ ለማስፈን አልማን መደገፍ::

አልማን ይደግፉ!

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ)
Amhara Development Association (ADA)

አድራሻ: በሀርዳር ስልክ: 058 220 0983 ፋክስ: 058 220 1088 ፖ.ሳ.ቁ. 307 e:mail ada.hq@ethionet.et
አዲስ አበባ ስልክ: 011 551 7886 ፋክስ: 011 551 7795 ፖ.ሳ.ቁ. 13685 e:mail ada.liaison@ethionet.et
www.amharada.org

‹‹ቀደም ሲል ሁለት እጁ እነሴ 46 የገጠር ቀበሌወች ነበሩት። አራቱ ወደ ከተማ አስተዳደር ተቀላቅለው የገጠር ቀበሌዎች 42 ሆነዋል። ‹‹ በዚህ ወረዳ 57,000 /አምሳ ሰባት ሺህ/ አርሶ አደር አባላት የማፍራት እቅድ ይዘን ነበር። አራቱ ወደ ከተማ በመሄዳቸው ምክንያት ከተቀሩት 42 ቀበሌዎች 49,531 አባላት አፍርተናል። ከእነዚህ አባላት በ2001 ዓ.ም

2,829,376 ብር /ሁለት ሚሊዮን ሥምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ብር/ ከአባልነት ዓመታዊ መዋጮ ሰብስበን ገቢ አድርገናል።

‹‹በሌሎች ወረዳዎች በእያንዳንዳቸው ከ14 ሺህ እስከ 35 ሺህ የሚቆጠሩ አባላት አሉን። በአጠቃላይ በዞኑ ከሚገኙት 18 ወረዳዎች አርሶ አደር አባሎች ያበራከትነው በአስራ ሁለቱ ነው። ከፍተኛውን የአባላት ቁጥርና የገንዘብ መዋጮ መጠን የሚይዘው ግን ሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ነው።››

ከአቶ ሥመወርቅ መንግሥቱ በተረዳነው መሠረት፣ በ2000 ዓ.ም የአልማ 6ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲካሄድ "በክልሉ ውስጥ አንድ ሚሊዮን አባላትን ማፍራት አለብን" የሚል መልዕክት ከማህበሩ የቦርድ ሊቀ-መንበር በኩል መልዕክት ተላልፎ ነበር። ከዚያ በፊትም ግን ዞኑ አወበል፣ አነደድ እና ደብረ ኤልያስ በተባሉት 3 ወረዳዎች አባላት ነበሩት። ይህን መነሻ በማድረግ በሌሎች ወረዳዎችም ግብር የሚከፍሉ አርሶ አደሮችን በሙሉ አባል ለማድረግ የሚያስችል እቅድ ሊነድፍ ችሏል። በእቅዱ አፈፃፀም ላይም የዞኑና የወረዳዎች የአስተዳደር አካላት ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል።

በቅድሚያ ውይይት የተደረገው ከቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቃነመናብርትና የጎጥ መሪዎች ጋር ነው። በዚህም ስለ አልማ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ማስያዝ መቻሉንና ራሳቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ይዘው መሰማራታቸውን ነው አቶ ሥመወርቅ ያብራሩልን።

በየገጠሩ ቀበሌዎች ከአርሶ አደሩ ጋር ስብሰባ እየተደረገ ውይይት በተደረገ ጊዜም ተቀባይነት ለማግኘት ችግር አልገጠማቸውም። በአንድ ቀበሌ ብቻ በአርሶ አደሩ ሳይሆን አወያይ ሆነው በተመደቡ ሰዎች የተፈጠረ ችግር ቢያጋጥምም ማስተካከያ ተደርጎበት ችግሩ ሊፈታ ችሏል።

ከአርሶ አደሩ ጋር በተደረገ ምክክር የተደረሰበት ውሳኔ ምን እንደነበርና ውሳኔው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ይገልፁልን ዘንድ ጠይቀናቸውም እንዲህ ነበር ያሉን።

‹‹አርሶ አደሩ አልማን የራሱ የልማት አካል አድርጎ በመውሰዱ፣ እያንዳንዱ አርሶ አደር በዓመት 36 ብር መዋጮ ሊያደርግ ተስማማ። የዚህን ዓመትም ሙሉ በሙሉ ከፍሏል።

‹‹የሚሰበሰበው ገንዘብ ለምን አገልግሎት እንደሚውል ለአርሶ አደሩ ተገልፆለታል።በአልማ አሰራር መሰረት፣ በአንድ ወረዳ ውስጥ ከማህበሩ አባላት ከሚዋጣ ገንዘብ 70 ከመቶው በዚያው በወረዳው ውስጥ ለልማት ይውላል። በዚህ ወቅት የሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ቀዳሚ የልማት ጥያቄ የሆነው ቀራንዮ ከተማ ላይ

አንድ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መገንባት ነው። ከተዋጣው ሰባ ከመቶው ገንዘብ ለዚህ ተግባር ይውላል።"

ከአቶ ሥመወርቅ መንግሥቱ ባገኘነው መረጃ መሠረት፣ የወረዳው ዋና ከተማም በዙሪያው የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎችን ጨምሮ ራሱን የቻለ ወረዳ ሆኖ ተዋቅሯል። ከዚህም 6001 የአርሶ አደር፣ 704 የከተማ ነዋሪዎችና 279 የመንግሥት ሠራተኞች የአልማ አባል ሆነዋል። አርሶ አደሮቹ በዓመት 10 ብር፣ የከተማ ነዋሪዎች እንደየፍላጎታቸው ከ50 እስከ 100 ብር፣ የመንግሥት ሠራተኞች 2 ብር ለመክፈል ወስነው፣በዚህ ዓመት 40,114 ብር ገቢ አድርገዋል።

ከዚህ እንደምነረዳው፣ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ውስጥ በብዛት የአልማ አባል በመሆን ከፍ ያለ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የቻሉት በየዓመቱ 36 ብር ሊያዋጡ የወሰኑት አርሶ አደሮች ናቸው። እኛም "ለአርሶ አደሮች በዓመት 36 ብር መክፈል ከባድ ሆኖ አልታያቸውም ወይ?" የሚል ጥያቄ አንስተን፣ አቶ ሥመወርቅ የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል።

‹‹አርሶ አደሮች በዓመት 36 ብር መክፈል ከባድ ሆኖ አልታያቸውም፡፡ ‹36 ብር የአንድ ሳህን ጤፍ ዋጋ ነች› ሲሉም ገልፀዋል፡፡ ይህ የሆነው አካባቢው ትርፍ አምራች በመሆኑ አይደለም፡፡ ወረዳው ትርፍ አምራች ቢሆንም የአልማን ተልዕኮ ባይረዳና አልማንም የራሱ ማህበር አድርጎ ባይመለከት ኖሮ አምስት ሳንቲም ለማውጣትም ፈቃደኛ አይሆንም ነበር፡፡

‹‹እንዲያውም ይህን 36 ብር እንደ መነሻ ነው የቆጠሩት፡፡ በሚቀጥለው ዓመት እያንዳንዱ አርሶ አደር ከዚህ የተሻለ ለማዋጣትና ከፍ ያለ የልማት ተግባር ለማከናወን ዝግጁ ነው፡፡››

እነሆ፣ ‹‹ሁለት እጁ እነሴ›› ማለት ‹‹ሁለት እጁን አነሳ፣ ሁለት እጁን ዘረጋ›› ማለት ይመስላል፡፡ አልማ ደግ አስቦ ደግ የሚያደርግ የልማት አለቃ መሆኑን ልብ አለና ሁለት እጆቹን ዘረጋ እንጂ፣ ይህ ባይሆን ኖሮ በእርግጥም ሁለት እጁ እነሴ አንድ እጁንም ባልዘረጋ ነበር፡፡ አልማ የማይነቀል የልማት ምሰሶው ለመሆኑ በየቀዬው ምድሩ ከተከላቸው የልማት አውታሮች በስተቀር አስረጅ የማያስፈልገው በመሆኑ ነው በዓመት አንድ ሳህን ጤፍ መስፈር ያልከበደውና ከገለባ የቀለለ የሆነበት፡፡ አልማ ባከናወናቸው የልማት ሥራዎች ተኩራርቶ የማይቆምና ለላቀ ተግባር የታጠቀ ትልቅ የወደፊት ተስፋው እንደሆነም ነብይነትን የማይጠይቀውና ድንቅ አያያዙን አይቶ በራሱ ህሊና የሚፈርደው ገሀድ እውነታው ነው፡፡ ለዚህም ነው ነገ ከአንድ ሳህን በላይ ጤፍ ሊሰፍርና ለእጥፍ ድርብ ልማት ቃል መግባቱ፡፡

በአጠቃላይ በምሥራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ 264,882 የአርሶ አደር፣ 19,722 የመንግሥት ሠራተኞች፣ 3,854 የከተማ ነዋሪ እና 1,764 የተማሪ፣ በድምሩ 290,222 የአልማ አባላት አሉ፡፡ ከእነዚህም በዚህ ዓመት (2001 ዓ.ም) ብቻ 3 ሚሊዮን ያህል ብር ተሰብስቦ ገቢ ሆኗል፡፡